# ቀድመው ድምፅ ይስጡ።

# በፖስታ ድምፅ ይስጡ።

## የልዩ የድምፅ መስጫ ወረቀት ጥያቄዎች አሁን ተከፍተዋል።

## ኦክቶበር 19 ድረስ አይጠብቁ።

ማንኛውም ብቁ የአልበርታ መራጭ በፖስታ ድምፅ ለመስጠት ማመልከት ይችላል። ልዩ ምክንያት አያስፈልግም።

ከቤትዎ ሆነው ድምፅ ይስጡ፣ 10ሩንም የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ለመሙላት የሚያስፈልግዎትን ጊዜ ይውሰዱ፣ እና በድምፅ መስጫ ቀን ሊኖሩ የሚችሉትን ረጅም ሰልፎች ያስወግዱ።

በጥያቄ 10 ላይ

**በካናዳ ውስጥ መቆየት**

✓

በጥያቄዎች 1–9 ላይ

**አይ (NO)**

✓

# እውነታወችን ከተሳሳተ መረጃወች እንለይ

**የተሳሳተ መረጃ**

**ለአልበርታ ችግሮች ተጠያቂው ኢሚግሬሽን ነው።**

**እውነታ**

አዲስ መጤዎች የሥራ ባልደረቦቻችን፣ ጎረቤቶቻችን እና ጓደኞቻችን ናቸው። ይሰራሉ፣ ግብር ይከፍላሉ፣ የሥራ ክፍተቶችን ይሞላሉ እና ለኢኮኖሚያችን አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። በጤና እና በትምህርት ዘርፍ ያሉ የአልበርታ ችግሮች በአዲስ መጤዎች የተከሰቱ አይደሉም።

**የተሳሳተ መረጃ**

**ቋሚ ያልሆኑ ነዋሪዎች የጤና አገልግሎት፣ ትምህርት እና አገልግሎቶችን በነፃ ያገኛሉ።**

**እውነታ**

ቋሚ ያልሆኑ ነዋሪዎች እዚህ ይሰራሉ እና የሕዝብ አገልግሎቶችን ለመደገፍ የሚረዱ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር ግብር ይከፍላሉ። ለአንዳንድ አገልግሎቶች ብቁ ያልሆኑ ሰዎችም አስቀድመው ከኪሳቸው ይከፍላሉ።

**የተሳሳተ መረጃ**

**ለኦታዋ መልዕክት ለመላክ ብቻ ለመለያየት ድምፅ መስጠት እንችላለን።**

**እውነታ**

መለያየት እውነተኛ የኢኮኖሚ እርግጠኛ አለመሆንን ይፈጥራል። ንግዶች ኢንቨስትመንትንና ቅጥርን ሊያዘገዩ ይችላሉ። ሥራዎች ሊጋለጡ ይችላሉ። ቤተሰቦችም ቀጥሎ ምን እንደሚመጣ በመጠየቅ ሊቀሩ ይችላሉ። ሥራችንን እና የኢኮኖሚ ደህንነታችንን ለአደጋ ሳናጋልጥ ለአልበርታ መቆም እንችላለን።

**የተሳሳተ መረጃ**

**እነዚህ የሕዝበ ውሳኔ ድምፆች የአልበርታን ችግሮች ይፈታሉ።**

**እውነታ**

እነዚህ ድምፆች የቀዶ ጥገና መጠበቂያ ጊዜን አያሳጥሩም፣ የቤተሰብ ሐኪም እንዲያገኙ አያግዙም፣ ተጨማሪ መምህር ወደ ክፍል አያስገቡም ወይም የምግብ ግዢ ወጪዎን አያሳንሱም። በእውነት አስፈላጊ በሆኑት ጉዳዮች ላይ እናተኩር፦ የጤና አገልግሎት፣ ትምህርት፣ የኑሮ ወጪ፣ ሥራዎች እና ጠንካራ ኢኮኖሚ።

## በእነዚህ የሕዝበ ውሳኔ (ሪፈረንደም) ጥያቄዎች ዙሪያ ብዙ ጫጫታ አለ።

እውነታዎችን ከተሳሳቱና ከተዛቡ መረጃወች መለየት አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም ይኽ ምርጫ በእርስዎና በቤተሰብዎ፣ በሕዝብ አገልግሎቶቻችን፣ በሥራ ዕድሎዎች እና በአልበርታ የኢኮኖሚ ደህንነት ላይ እውነተኛ ውጤቶች ሊኖራቸው ይችላል።

# ይበቃል።

ከአሁን በኋላ አለመረጋጋት አይኖርም።

ከአሁን በኋላ ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮች አይኖሩም።

**ድምጽዎን ለመስጠት ቃል ይግቡ፦**

**ድምጽዎን ለመስጠት ቃል ይግቡ። በፈቃደኝነት ያግዙ። መዋጮ ያድርጉ። ይሳተፉ፡ albertareferendum2026.org**

በTogether – “No!” የተፈቀደ (Public Interest Alberta, 10512 122 St NW Edmonton)፣ የሕዝበ ውሳኔ (ሪፈረንደም) የሶስተኛ ወገን አስተዋዋቂ። ያግኙን፦ office(at)pialberta.org። በአልበርታ በካናዳ ውስጥ እንድትቆይ እንደግፋለን፣ እና ሌሎቹን ዘጠኝ ጥያቄዎች እንቃወማለን።

# ይበቃል።

→ ወደ ፊት

→→ እንራመድ።

**በኦክቶበር 19፣**

**የአልበርታ ነዋሪዎች በ10 የሕዝበ ውሳኔ (ሪፈረንደም) ጥያቄዎች ላይ ድምፅ ይሰጣሉ።**

የአልበርታ ቤተሰቦችን የእለት ተለት ሕይወት የሚነኩ ከዚህ ሕዝበ ውሳኔ (ሪፈረንደም) የላቁ በዙ ጉዳዮች አሉ፦ የጤና አገልግሎት፣ ትምህርት፣ የኑሮ ወጪ፣ ሥራዎች እና ኢኮኖሚያችን። ጊዜያችን፣ ጉልበታችን እና የግብር ገንዘባችን ለእነዚህ ጉዳዮች መዋል አለበት።

## ከአሁን በኋላ አለመረጋጋት አይኖርም።

## ከአሁን በኋላ ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮች አይኖሩም።

በጥያቄ 10 ላይ

**በካናዳ ውስጥ መቆየት**

✓

በጥያቄዎች 1–9 ላይ

**አይ (NO)**

✓

# ምን ላይ ነው ድምፅ የምንሰጠው?

**10 የተለያዩ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ይሰጡዎታል፦**

### Q1 — ኢሚግሬሽን

በኢሚግሬሽን ላይ የክፍለ ግዛቱን ቁጥጥር ማሳደግ፣ ኢሚግሬሽንን መቀነስ፣ ለኢኮኖሚያዊ ኢሚግሬሽን ቅድሚያ መስጠት እና ለአዲስ የሥራ ዕድሎች የአልበርታ ነዋሪዎችን ቅድሚያ መስጠት።

### Q2 — የሕዝብ አገልግሎቶች

በኢሚግሬሽን ሁኔታ መሠረት በክፍለ ግዛቱ የሚሰጡ የጤና፣ የትምህርት እና የማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነትን መገደብ።

### Q3 — የማህበራዊ ድጋፎች

ቋሚ ያልሆነ የኢሚግሬሽን ሁኔታ ላላቸው ሰዎች የ12 ወር የአልበርታ ነዋሪነት መስፈርት ማስቀመጥ።

### Q4 — ጤና አገልግሎት እና ትምህርት

ቋሚ ያልሆነ የኢሚግሬሽን ሁኔታ ላላቸው ሰዎችና ለቤተሰቦቻቸው የጤና አገልግሎትና ትምህርት አጠቃቀም ክፍያ ወይም ፕሪሚየም መጠየቅ።

### Q5 — ድምፅ መስጠት

በአልበርታ የክፍለ ግዛት ምርጫዎች ድምፅ ለመስጠት የካናዳ ዜግነት ማረጋገጫ እንዲቀርብ መጠየቅ።

### Q6 — ዳኞች

የኪንግስ ቤንች እና የአፒል ፍርድ ቤት ዳኞችን የመምረጥ ሥልጣን ከኦታዋ ይልቅ ለክፍለ ግዛት መንግሥታት መስጠት።

### Q7 — ሴኔት

የፌዴራል ሴኔትን ለማስወገድ ሕገ-መንግሥቱን ማሻሻል።

### Q8 — የፌዴራል ፕሮግራሞች

ክፍለ ግዛቶች በክፍለ ግዛታዊ ሥልጣን ውስጥ ካሉ የፌዴራል ፕሮግራሞች ጋር ተያይዞ የሚሰጣቸውን የፌዴራል ድጋፍ ሳያጡ ከእነዚህ ፕሮግራሞች ለመውጣት እንዲችሉ ማድረግ።

### Q9 — የክፍለ ግዛት ሥልጣን

በክፍለ ግዛት ወይም በጋራ ሥልጣን ባላቸው ጉዳዮች ላይ የክፍለ ግዛት ሕጎች ከፌዴራል ሕጎች ጋር ሲጋጩ ቅድሚያ እንዲኖራቸው ማድረግ።

### Q10 — መለያየት

በካናዳ ውስጥ መቆየት ወይም ወደፊት ስለመለያየት አስገዳጅ ሪፈረንደም ለማካሄድ የሚያስፈልገውን የሕግ ሂደት መጀመር።